empowering youth

# Yes I Do project



# ወጣትነትና

## የስነተዋልዶ ጤና ገጽታዎች

TALENT YOUTH ASSOCIATION

inspire. support. empower.




# ጾታዊ መብቶች (sexual rights)

ሁሉም ሰው ያለ ጥቃት፣ ያለ መሳቀቅ ያለ መሳቀቅ የሚከተሉት መብቶች አሉት

- የላቀና ሊደርስበት የሚችል ወሳኝ ፆታዊ ጤንነት ማግኘት
- ስለ ሩካቤ-ስጋና ሌሎች ፆታዊ ጉዳዮች መረጃ መጠየቅ፣ ማግኘትና ማስተላለፍ
- የፍቅር (የግብረ-ሥጋ ግንኙነት) አጋር መምረጥ
- ወሲብ ለማድረግና ላለማድረግ መምረጥ
- በፍቃደኝነት ላይ የተመሰረተ ፆታዊ ግንኙነትና ጋብቻና አርኪ፣ ጤነኛና አዝናኝ የሆነ ግብረ- ሥጋ ግንኙነት

# የስነ-ተዋልዶ

**ጤና ማለት የህመም ወይም የስቃይ ስሜት አለመሰማት ብቻ ሳይሆን በተለይም በአካላዊ፤ በአእምሮአዊ ፤ በመንፈሳዊ እንዲሁም በማህበራዊ ህይወታቸው ውስጥ ከስነተዋልዶ ጤና ጋር ተያያዥ በሆኑ ጉዳዮች ማለትም የመራቢያ አካላትን ደህንነት፤ ጥቅም እና ሁለንተናዊ ሂደት ትክክለኛ ወይም ያልተዛባ መሆንን ያካትታል።**

በመሆኑም የስነተዋልዶ ጤና ሲባል አንዲት ሴት ወይንም ወንድ እንደፍላጎታቸው እንደምርጫቸው ጥንቃቄ የተሞላበት የግብረስጋ ግንኙነት በማድረግ ህይወታቸው በሰላም የመምራት ቁልፍ ዘዴ ነው።

በመሆኑም ወጣቱ የህብረተሰብ ክፍል ለስነተዋልዶ ጤና ችግሮች ተጋላጭ እዳይሆኑ በቅርብ ከሚገኙ ጤና ተቋማት እንዲሁም ወጣት ማእከላት በመሄድ ወቅታዊ የሆኑ እንዲሁም ውሳኔ ላይ ለመድረስ የሚረዱ የመፍትሄ

## የስነተዋልዶ ጤና መብቶች

**አለምአቀፍ ሰብአዊ መብት ማእቀፎችን ጨምሮ በአለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ድንጋጌዎች የተካተቱ መብቶች ከዚህ እንደሚከተለው ተቀምጠዋል**

- **የመኖር መብት፡-** በእርግዝና ምክንያት የማንኛዋም ሴት ህይወት አደጋ ውስጥ መውደቅ የለበትም
- **የነጻነትና ደህንነት መብት፡-** ማንኛዋም ሴት ለግርዛት፣ ላልተፈለገ እርግዝና ለውርጃ መዳረግ የለባትም
- **የግል ሚስጥርን የመጠበቅ መብት፡-** ሁሉም የሥነ-ወሲብና ተዋልዶ ጤና አገልግሎቶች የተገልጋዩን መረጃ በሚስጥር የመጠበቅ እንዲሁም ሴቶች በምርጫቸው የተዋልዶ አገልግሎት የማግኘት መብት
- **ሀሳብን በነጻነት የማራመድ መብት፡-**በሥነ- ወሲብና ተዋልዶ ጤና ዙሪያ በነጻነት ሀሳብን የማራመድ መብትን መረጃና ትምህርት የማግኘት መብት፡-
- **የሥነ-ወሲብና ተዋልዶ ጤና፣** የጽንስ መከላከያ ዘዴዎች ውጤታማነት፣ ጠቀሜታና ተጓዳኝ ችግሮችን በተመለከተ በቂ መረጃ የማግኘትመብት፣
- **የወሲብ ደህንነት፣** የተዋልዶ ጤናና መብቶች ቀዳሚ ትኩረት እንዲያገኙ የመጠየቅና የመቃወም መብት
- **በእኩልነት የመኖር መብት** የወሲብና ተዋልዶ ህይወትን ጨምሮ ከማንኛውም አይነት አድሎና መገለል የመጠበቅና ነጻ የመሆን መብት
- **ጋብቻን ለመፈጸምና ላለመፈጸም ወይም ቤተሰብ ለመመስረትና ለማቀድ የመወሰን መብት**
- **የመውለድ እና የቤተሰብ ዕቅድ የመጠቀም መብት፡-** ማንኛውም ሰው ምን ያህል ልጅ በምን ያህል ጊዜ በማራራቅ መውለድ እንዳለበት በነጻነት እና በኃላፊነት በተሞላበት ሁኔታ የመወሰን መብት ይኼም መቼ እንደሚወልድ እንዲሁም መብቱን የመጠቀም ብቃትን ያካትታል
- **ሁሉም ሴቶች፣ ወንዶች እና ወጣቶች እራሳቸውን ከሀይል ጥቃትና ከወሲባዊ ብዝበዛ የመከላከል መብት አላቸው**
- **የጤና እንክብካቤ የማግኘት መብትና** ለጤና ጎጂ ከሆነ ልማዳዊ ድርጊቶች ነጻ የመሆን መብት

## የስነተዋልዶ
# ጤና ችግሮች

*በወጣትነት እድሜ ክልል ማለትም 15-24 አመት ከሆኑ ሴቶች 36% ያክሉ የቤተሰብ እቅድ አገልግሎት ተጠቃሚ ናቸው። እንዲሁም 20% የሚሆኑት ወጣት ሴቶች የቤተሰብ እቅድ መጠቀም እየፈለጉ በተለያየ ምክንያት መጠቀም ያልቻሉ ናቸው።*

## የአፍላ እድሜ እርግዝና

- የአፍላ እድሜ እርግዝና በአለም የጤና ድርጅት ትርጓሜ መሰረት 20 አመት እድሜ ሳይሞላቸው የሚፈጠር እርግዝና እና ወሊድን ያካትታል።
- ከዚህ ጋር ተያይዞ 70000 ያክል በአፍላነት የእድሜ ክልል የሚገኙ ሴቶች ከእርግዝና እና ከወሊድ ጋር ተያይዞ በሚከሰት ችግር ህይወታቸው ያልፋል።



በኢትዩጲያ 13% ሚሆኑት ሴቶች ከ15-19 እድሜያቸው ልጅ ይወልዳሉ።

## ያለ እድሜ ጋብቻ

- የኢትዩጵያ ቤተሰብ ሕግ እንደሚደነግገው ማንኛውም ሰው ሴት ወይም ወንድ ጋብቻ መፈፀም የሚችለው እድሜው 18 እና ከዛ በላይ እድሜ ሲሆን ነው።
- Demographic Health Survey 2016 ይፋ ባደረገው ጥናት በኢትዩጵያ ሴቶች ጋብቻ የሚፈጽሙበት አማካኝ እድሜ 16.1 ነው።
- አማራ ክልል የሚያገቡ ሴቶቹ እድሜ በጣም ዝቅተኛ ከሆኑ ክልሎች ቀዳሚውን ስፍራ ይይዛል።
- ጥናቶች እንደሚያመላክቱት የልጃገረዶች ትምህርት በተለይም የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ተሳታፊነት እና ተጠቃሚነትን ማሳደግ ጋብቻንና የመጀመሪያ እርግዝናን እንዲዘገይ ያደርጋል።



**በኢትዩድያ 13% የሚሆኑት ሴቶች ከ15-19 እድሜያቸው ልጅ ይወልዳሉ።**

በ

Yes I Do project

## እየተከናወኑ ያሉ ተግባራት

## ከፖሊሲ አንጻር

- ያለእድሜ ጋብቻ የአንድ ሃገር የድህነት መለኪያ ተደርጎ ይወሰዳል
- እድሜያቸው ለትምህርት የደረሰ ሴቶች በትምህርት ገበታቸው ላይ

እንዲገኙ እና በተገቢው መንገድ ወጣቶች በስነጾታዊ ጉዳዩች ላይ በቂ የሆነ መረጃ ትምህርታቸው እንዲከታተሉ ድጋፍ እነንዲያገኙ ማስቻል ማድረግ

- በትምህርት ካሪኩለመሙ ውስጥ comprehensive sexual education እንደአንድ የትምህርት ክፍለጊዘዜ ተካቶ ትምህርት እንዲሰጥ ማድረግ
- ሴቶችች በማህበረሰቡ ውስጥ የሚኖራቸውን የኢኮኖሚ ድርሻ በማሳደግ እራሳቸውን በገቢ በማሳደግ በራሳቸው የመወሰን አቅም

# የስነተዋልዶ ጤና አገልግሎቶች

- ቤተሰብ እቅድ አገልግሎት (የእርግዝና መከላከያ) ምክር፣ መረጃ እና ትምህርት መስጠት
- መሀንነትን መከላከል እና ማከም
- ህጋዊ እና ንጽህናው የተጠበቀ የጽንስ ማቋረጥ አገልግሎት
- ስለ ግብረ ስጋ ግንኙነት የማማከር አገልግሎት
- የአባላዘር በሽታ ምርመራና ህክምና
- ጾታዊ ጥቃት የደረሰባቸውን ሴቶች ምርመራና ህክምና
- የኤች አይቪ ምርመራና ህክምና አገልግሎት

**P.O.box:** 2187 Code 1110 Addis Ababa, Ethiopia
**Tel:** +251116184220 **E-mail:** contact@tayaeth.org | www.tayaeth.org

© 2018 Talent Youth Association. All rights reserved.